የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፰ ቀን
፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.24
ADDIS ABABA , 8th January 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፯/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለጣና በለስ የተቀናጀ የውሃ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ................................ገጽ ፰ሺ፯፻፵፰

CONTENTS

Proclamation No. 917/2015

International Development Association Additional Financing Agreement for the Tana Beles Integrated Water Resources Development Project Ratification Proclamation ..............................page 8748

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፯//፪ሺ፰ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኀበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጣና በለስ የተቀናጀ የውሃ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፫ ሚሊዮን ፯፻ ሺ. ኤስ ዲ አር (ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ. ኤስ ዲ አር) የሚያስገኘው ተጨማሪ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ፲፩ያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በህገ መንግስቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 917/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANACING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association providing to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 3,700,000 SDR (three million seven hundred thousand Special Drawing Rights) Additional Financing for Tana Beles Integrated Water Resources Development Project signed in Addis Ababa on the 22nd day of October;

**WHEREAS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 8th day of December 2015;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ለጣና በለስ የተቀናጀ የውሃ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፯/፪ሺ፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5715 —ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫ ሚሊዮን ፯፻ ሺ ኤስ ዲ አር (ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as the “International Development Association Additional Financing Agreement for the Tana Beles Integrated Water Resources Development Project Ratification Proclamation No.917/2015”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Credit Number 5715-ET signed in Addis Ababa on the 22nd day of October 2015 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 3,700,000 SDR (three million seven hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. <u>Effective Data</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 8th day of January 2016**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**